# ወረቀት ከዕርሳስ ይከብዳል

አብርሃም በየነ

ሞርታረና ቢአር ተጠምደው ሲያጎሩ

ቦቃ- ዕሳት ሲተፉ ሲቃጠል አየሩ፤

ተራሮች ሲናዱ ሲደረመስ ምድሩ

ወንዞች ቀይ ሲቀልሙ እፅዋትም ሲያርሩ፤

በጦርነት እቶን የሰው ህይዎት ሲጋይ

የማንንም ህይዎት ሳይጥል አደጋ ላይ

ወረቀት ይከብዳል በሚጥለው ግዳይ፤

የብዕሩ ጫፍ-ጦር የሚኩለው ፅዳል

ሺህ ጊዜ ወረቀት ከእርሳስ ይከብዳል።

# ፍትህ በዚህች ዓለም

የተረገጠ ህዝብ በግፈኞች ጫማ

ፍትህ የተራበ ፍትህ የተጠማ፤

ታንጎ እየደነሰች እላዩ ላይ ቆማ

ለምታስገብረው ህይዎት ለከራማ

ለዓለም አቤት ይላል በደሉን ሊያሰማ።

# ርሃብና ድንጊያ

ሰማይ ጠቀስ ህንፃ የድንጊያ ካብ ውበት

በጎዳና እያዩ በተንጣለለ አስፋልት፤

ህዝብ በየ ቀኑ ሺህ በርሃብ ሲሞት

ምን አማርኛ ነው ፤ አገር አድጓል ማለት?

ህዳር 2004